ቡሄ/ሖ/ ዘውእቱ በዓለ ኖሎት ወደቀ መዛሙርት

/ሐጉስ ዘማርያም/

ከዘጠኙ የጌታችን ዐበይት በዓላት አንዱ የሆነው የደብረ ታቦር በዓል በምእመናን ዘንድ ቡሄ/ሖ/ ይባላል። የሁኔታና የድርጊት አፈጻጸም ገላጭ የሆነው የዚህ ስያሜ መሠረተ ቃል በልዩ ልዩ ዐውደ ሐሳብ /አስተያየት/ ሲብራራ ይገኛል። ይኸውም :–

ቡሄ :– ተብሎ በሃሌታው «ሀ» ኀምስ ሆሄ /ቡሄ/ ሲጻፍ የበራ፣ የደመቀ፣ የጐላ፣ ብርሃን፣ የብርሃን በዓል ማለት ይሆናል። በሌላም በኩል ጸቡቴ /ጸቦት የችቦ ስም ነው/፣ ችቦዬ፣ መብራቴ ማለት ነው። /አዲሱ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 95 እና 234/። ይኸም በቅዱስ ማቴዎስ፣በቅዱስ ማርቆስ፣ በቅዱስ ሉቃስ ወንጌል እንደተገለጠው በታቦር ተራራ ላይ የጌታ ገጹ በሦስት አዕማደ ሐዋርያት ፊት እንደ ፀሐይ በማብራቱ፣ልብሱም «አጣቢ በምድር ላይ ሊያነጣው እስከማይችል» ድረስ በጣም ነጭ፣ አንጸባራቂ በመሆኑ ነው። /ማቴ. 17፥2፣ማር.9፥3፣ሉቃ.9፥29/።

ይህንንም በማስመልከት በበዓሉ ዋዜማ /ነሐሴ 12 ቀን/ ችቦ ይበራል። በብሔራዊው የልጆች ጨዋታም «ቡሄ ና ፥ ቡሄ በሉ፤ ቡሄ በሉ ልጆች ሁሉ ፥ ቡሄ በሉ ዝም አትበሉ፤ ቡሄ መጣ፣ ያ መላጣ፣ ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ፣ አንዱን አምጪው አታማርጪው፣ አንዱን አምጪው ያን መላጣ፣ ቅቤ ቀቢው እንዳይነጣ...» ይባላል። «ቡሽ ዬ» ተገለጠ፣ነጣ፣በራ ሆነ፤ «መቡሽ የት» ራስ ገላጣ መሆን ማለት ነው። ራሰ በራን ሰው «ቡሃ ራስ» እንዲሉት።

በሌላው ብሂላችንም «ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት፣ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት» የምንለውም በኢትዮጵያችን ወቅቱ የፀዓተ ክረምት ዋዜማ ስለሆነ፤ ክረምቱ አፈናው ተወግዶ /ተጋምሶ/ የብርሃን ወገግታ የሚታይበት፤ በዶፉና በጎርፉ ስትዋልል የነበረች መሬት የምትጸናውና የምትረጋው /የመሬት መንሸራተት አይኖርም/ በዚሁ በዓል አካባቢ ስለሆነ ነው። ድርጊቱ በተፈጸመበት /ጌታ ብርሃን መለኮቱን በገለጠበት/ በፍልስጥኤም ግን የደመና መልክ የማይታይበት ፍጹም የበጋ ወራት ነው። /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣1986 ዓ.ም፣ ገጽ 127/።

ቡሔ :– ተብሎ በሐመሩ «ሐ» ኀምስ ፊደል /ቡሔ/ ሲጻፍ ደግሞ «ደስታ፣ ፍሥሓ» ማለት ይሆናል። «ታቦርና አርሞንዔም በስምከ ደስ ይላቸዋል፣ታቦር ወአርሞንዔም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ» /መዝ.88፥12/ ተብሎ በቅዱስ ዳዊት በተነገረው ትንቢት መሠረት የጌታ መለኮታዊ ብርሃን ከታቦር እስከ አርሞንዔም ተራራ ድረስ ታይቷል። ይህ መለኮታዊ ብርሃን በወረደበት ዕለት፣ በታቦርና በአርሞንዔም አካባቢ መዓልቱ የሌሊቱን ቦታ ስለ ወሰደው ከብቶቻቸውን በመስክ ዙሪያ ላይ የሚጠብቁ እረኞች በሁኔታው ሐሴት አድርገዋል።

ቡሓ :– የሰላምታና የቡራኬ ቃል ሲሆን «ፍሥሓ፣ሰላም» ማለት ይሆናል። ይኸውም በሚያዩት መለኮታዊ ብርሃን በደስታ ተሞልተው እንደወጡ የቀሩት፣ ከላይ የተጠቀሱት ኖሎት /እረኞች/ ወላጆች ምግባቸውን ይዘው ካሉበት ሄደው «ቡሓ» ብለዋቸዋል። ትርጉሙም «እንዴት ዋልክ ፥እንዴት አደርክ ፥ጤና ይስጥክ፣ደስታ ሰላም ላንተ ይኹን፣ጠላትክን ያውድቅ፣ቢሰኛክን ያርቅ» ማለት ነው። /ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፥ገጽ 260/።

ብሔ :– አንድም ልጆቹን /እረኞቹን/ ወላጆቻቸው ብርሃናዊውን ክስተት «ምንድን ነው?» ቢሏቸው «ብሔ» ብለዋል። ይኸውም በዕብራይስጥ ቋንቋ «አምላክ» ማለት ነው። እንግዲህ ይኸው ቃል ከጊዜ ብዛት ወደ ቡሔ የተወለጠ ይመስላል።

ብሁዕ :– ያልቦካ ያልኮመጠጠ ማለት ነው። «አብህአ» አቦካ ፥ «ብሁዕ» ካልቦካ ሊጥ /ቡሆ/ የሚጋገር ቂጣ ማለት ሲሆን ይኸውም አንዳንዶች በአሪቱ እሥራኤል ዘሥጋ ያከብሩት ከነበረው የእሸት ወይም የቂጣ በዓል /ኦ.ዘሌ. 23፥14፥19/ ሲያያዝ የመጣ ነው በማለት ሲያትቱ «በዚህ ወር አጋማሽ አርሶ አደሩ ከነበረው ሰሬፍት ያደርጋል፤ በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች /የበልግ አዝመራ በሚደርስባቸው ሥፍራዎች/ አዲስ እህል ይቀመሳል፤ «የጐመን ምንቸት ውጣ፥የገንፎ ምንቸት ግባ» እንዲሉ። ይህም «ቡሄ» ይባላል፤ ትርጉሙም «ብሁዕ»፥ያልቦካ ማለት ነው። የሚደገፍ አስተያየት ነው፥ ምክንያቱም የሚጋገረው ያልቦካ ቂጣ በመሆኑ ነው። /ኦ.ዘጻ.16፥1–12/። እሥራኤል ዘሥጋ ከፋሲካ በዓል በኋላ ሰባት ሱባኤ ቆይተው በሚያከብሩት የመከር በዓል /በዓለ ሠዊት/ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ያልቦካ ቂጣ /እርሾ የሌለበት/ ለመከራቸው በኩራት ነዶ /አዲስ የእህል ቁርባን/ መታሰቢያ ነው። /ኦ.ዘሌዋ.23፥1–16፣ኦ.ዘኍል 28፥26/። /ሐና ቤተ ክርስቲያን ዘኢ-

www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ ቀዳሚት፥ 23ኛ ፥ዓመት ቁጥር 22፥1960 ዓ.ም./።

እንደ ፊለጎ የርጳኖስ ሁሉ ደብረ ታቦር ጌታ ክብረ መንግሥቱን ብርሃነ መለኮቱን ለነቢያትና ለሐዋርያት የገለጠበት ቅዱስ ተራራ ነው። /2ጴጥ.1፥16–19/። ከነቢያቱ ለሊቀ ነቢያት ሙሴ «ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም።» /ኦ.ዘጸ.33፥28/ በተባለው መሠረት «እባክህ ክብርህን /ፊትህን/ አሳየኝ፤» /ኦ.ዘጸ.33፥19/ የሚለውን የባለሟልነት ጥያቄውን መልሶለታል። በጀርባ የተመሰለው ከ5500 ዘመን በኋላ የተፈጸመው ምሥጢረ ሥጋዌ ነው። እንድም በፊልጶስ ቂሣርያ ጌታ ሐዋርያትን «ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ብለው ይሉታል?» ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ «ሙሴ ነው ይሉሃል» ብለው ነበርና፤ «እግዚእ ሙሴ ፥አምላኩ ሙሴ» መሆኑን ለማስመስከር ሙሴ ከመቃብር ተጠርቷል። /ማቴ. 16፥14፣17፥3/። የቃል ነቢያት ከሚባሉት መካከል ኤልያስ ከብሔረ ሕያዋን የተጠራው «የኃይል ሥራ ህን ተመልክተው ኤልያስ ነህ ይላሉ» ስላሉት «እግዚእ ኤልያስ፥ አምላኩ ኤልያስ» መሆኑን ለማስመስከር ነው።

ከሐዋርያትም ለሦስቱ «አዕማደ ሐዋርያት፥ የምሥጢር ደቀ መዛሙርት» /ገላ.2፥9/ በፊልጶስ ቂሣርያ በዕብራይስጡ ኬፋ፥በግሪኩ ጴጥሮስ በግእዙ ኰኲሕ /አለት/ የተባለውን የዮና ልጅ ስምዖንን ምስክርነት /ማቴ.16፥16/ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው» /ማቴ.17፥5/ በሚለው በባሕርይ አባቱ በአብ ምስክርነት አስረግጦላቸዋል። በዚህም በልባቸው ጥርጥርንና ፍቅረ ሢመትን ያሳደረ ዲያብሎስን ድል ነስቶላቸዋል። መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ሲገልጥላቸው «አይሁንብህ» ያለው ስምዖን ወልደ ዮና «እርሱን ስሙት» በሚለው መለኮታዊ ድምፅ ተገሥጸአል።

ከዚህ በመነሣት ነው ደብረ ታቦር ወይም የቡሄ/ሖ/ በዓል የደቀ መዛሙርትና የእረኞች በዓል ነው የሚባለው። እረኞች በየሚሄዱበት ጎጆ ሠርተው ከወላጆቻቸውና ከየዘመዶቻቸው የወሰዱትን ኅብስት /ሙል ሙል ዳቦ/ በኅብረት በመመገብ በደመና በተሰማው ድምፀ መለኮት አምሳል ከበዓሉ ቀደም አድርገው የገመዱትን ጅራፍ በማጮኸት /በማጮኽ/ መለኮታዊውን ብርሃን ለማመልከት ችቦ በማብራት በታላቅ ደስታ

ያከብሩታል።

ኅብስቱ /ሙልሙል ዳቦው/ በታቦር ተራራ ዙሪያ ለነበሩት እረኞች ወላጆቻቸው ምግባቸውን ይዘው መሄዳቸውን ያጠይቃል። እንድም ኅብስቱ ምሳሌነቱ ለክርስቶስ ነው፤ 'አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት፤ እኔ ከሰማይ የወረድኩ የሕይወት እንጀራ ነኝ' እንዳለ። /ዮሐ.6፥32–59/።

ልጆቹ ዳቦአቸውን ከመግመጥ ጋር በጅራፍ ሲጋረፉ ይውላሉ። ለግርፊያው ተምሳሌት ባይገኝለትም ጅራፉ ሲጮኽ ማስደንገጡ ሦስቱ አዕማደ ሐዋርያት /ጴጥሮስ፥ያዕቆብና ዮሐንስ/ በድምፀ መለኮት መደንገጣቸውንና መውደቃቸውን ያስታውሳል። እዚህም ላይ የጅራፉን ድምፅ ነጎድጓዳዊ ለማድረግ የሚጮኸው በፈፋና በተራራ ላይ እንጂ እንደ ዛሬው በየከተማውና በየመንደሩ ተላላፊ መንገደኛውን ሁሉ በማወክ አልያም ከትውፊታችን ውጭ በሆነ መልኩ ዘመን ያፈራውን ተቀጣጣይ ርችት በማፈንዳት፥ በየእግረኛ ማ ማ፥ኪስና ቦርሳ ውስጥ እየጣሉ በማስደንገጥ አለመሆኑን ልብ ይሏል።

ዳግመኛም ወላጆች በታቦር ተራራ ዙሪያ የነበሩትን ልጆቻቸውን ለመፈለግ ችቦ እያበሩ ሲሄዱ ልጆቹም ጅራፍ በማጮኽ ያሉበትን ሥፍራ መጠቆማቸውን ያስረዳል። በከተሞች አካባቢ በዋዜማው ነሐሴ 12 ቀን የሠፈር ሕፃናት በየቤቱ እየዞሩ ይጨፍራሉ። የሚገጥሙትም ግጥም አላቸው። ከግጥሙም በጥቂቱ፡–

«ሆያ ሆዬ ሆ ሆያ ሆዬ
ሆይ የኔ ጌታ ሆይ
የእኔማ እገሌ ሆ የሰጠኝ ሙክት
ነጭማ ነው ሆ ባለምልክት
መስከረም ጠባ ሆ እርሱን ሳነክት
እዝ...
እዚያ ማዶ ሆ ጭስ ይጨሳል
አጋፋሪ ሆ ይደግሳል
ያችን ድግስ ሆ ውጬ ውጬ
በድንክ አልጋ ሆ ተገልብጬ
ያች ድንክ አልጋ ሆ ዓመለኛ
አላንድ ሰው ሆ አታስተኛ
እዝ...» የሚል ነው።

«ሆዬ፥ሆያ ሆዬ» የሚለው ቃል «ጌታዬ ሆይ፥እመቤቴ ሆይ...» እያሉ አባወራውን ወይም እማወራዋን የሚያከብሩበትና የሚያቆላምጡበት የፍቅር አጠራር ነው። «ሆ» የሚለው አዝማች ፊደልም «አሆ በልዎ ለክርስቶስ፥ ሐሰ በልዎ ለዲያብሎስ» /ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙ/ /ያዕ.4፥8/ እንዲል በታቦር ተራራ ላይ እግዚአብሔር አብ ለባሕርይ ልጁ ለእግዚአብሔር ወልድ «ልመለክበት የወደድሁት፥ለተዋሕዶ የመረጥኩት ልጄ ይህ ነው፤ እሞታለሁ ቢላችሁ፤ አትሞትም አይሁንብህ አትበሉት፤ እሺ በጁ በሉት» ያለውን የትእዛዝና የተግሣጽ ቃል ያስታውሳል። ቀደም ብሎ በማቴ.16፥21–23 እንደምንመለከተው ጌታችን «ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው» ለደቀ መዛሙርቱ ሲገልጥላቸው በነገር ሁሉ ከሐዋርያት ፊጣን የሚሆን ጴጥሮስ ስለ ፍቅሩ ሳስቶና ተናድዶ «አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ክፉ አይደርስብህም» ብሎ ሲገሥጸው /ሲያሳብለው/ ጀመረ። ጌታችንም ወደ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ «አንተ ሰይጣን ባለጋራዬ፥ወግድ ከወደ ኋላዬ፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና፥ዕንቅፋት ሆነህብኛልና» አለው። ትርጓሜ ወንጌል ዘማቴዎስ ይህንን ሲያብራራ «...ጽኑ ባለጋራዬ ሲል ነው፤ ከወደ ኋላ ራስ አይቶ የሚመጣ ጠላት ጽኑ ባለጋራ ነውና። ... አንድም የምእመናን የነቢያት ጽኑ ባለጋራቸው ሲል፥ ጌታችን አይሙት ማለት ነቢያትን ሐሰተኞች ማድረግ ነውና፥ ምእመናን አይዳኑ ማለት ነውና። አንድም በማቴ.16፥16 ላይ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅነቱን ሲመሰክር «አንተ ብፁዕ ነህ» ቢለውም አሁን ደግሞ እንደ ጊዜ ግብሩ ተመልሶ «ሑር፥ ወደኋላዬ ሂድ፣አንተ ሰይጣን » ብሎ በጴጥሮስ አንጻር ሰይጣንን ገሠጸው። በቢታንያ በበለስ አንጻር ኃጢአትን እንደ ረገማት። /ማቴ.21፥19/።

«የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና፣እንቅፋት ሆነህብኛልና» ሲልም ሞቶ ፈርሶ በስብሶ ይቀራል ትላለህ እንጂ ይነሣል አትለኝምና። አንድም «ከሰው ሹመት ሽልማት ትሻለህ እንጂ እግዚአብሔር የሚያወርስህን ክብር አትሻምና» ሲለው ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ጌታን ምድራዊ መሲሕ አድርገው በማሰብ ቀኝ ጌትነትንና ግራ ጌትነትን በእናታቸው በኩል የለመኑት የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ በማይገባ ስእለታቸው ተግሣጽ አግኝቷቸዋል። /ማቴ.20፥20–28/።

ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና በልጆቹ ዝማሬ ላይ «አጋፋሪ» የተባለው መልአከ ኃይሉ ለልዑል የሆነው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው፤ «ጭሱ» ደመና፥ «ድግሱ» መና፥ «ድንክ አልጋ» የተባለችውም ማርና ወተት የምታፈስሰው የተስፋዪቱ ምድር /ምድረ ከነዓን/ ናት። /ኦ.ዘፍ.12፥7፣ኦ.ዘጸ.3፥8/። ይህም በ40 ዓመቱ የእሥራኤል ዘሥጋ ጉዞ መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤል ከፊት እየቀደመ ቀን ቀን በዓምደ ደመና ሌሊት ሌሊት በዓምደ እሳት እየመራ በደመና ዓይበት ቋጥሮ መና እያወረደ እያበላ፣ውኃ ከጭንጫ አፍልቆ እያጠጣ ምድረ ርስትን እንዳወረሳቸው ያመለክታል። /ኦ.ዘጸ.23፥20፣14፥19–20፣16፥13–36፣17፥1–7/።

«ያች ድንክ አልጋ ዓመለኛ፥ አላንድ ሰው አታስተኛ» መባሉም በክፉ ወሬ፥በመጉምጀት፥ በአምልኮተ ጣዖት፥ በዝሙት፥በሐሜት /በማንጎራጎር/ ምክንያት ከምድረ ግብጽ የባርነት ቤት ከወጡት ከግማሽ ሚልዮን በላይ /600,000 ያህል/ እስራኤላውያን መካከል ለምድረ ርስት ሳይበቁ /ሊቀ ነቢያት ሙሴም ሳይቀር/ በሲናይ በረሃ መቀሰፋቸውንና መሞታቸውን ፤ በእግዚአብሔር ጥበቃና መግቦት እምነታቸውን ያሳረፉት የዮፎኒ ልጅ ካሌብና የነዌ ልጅ ኢያሱ ብቻ ቅድስት ሀገርን መውረሳቸውን ይተረጉማል። /ኦ.ዘኁል.14፥26–30 እና 38/።

ይህን በመልአክ እጅ የተደረገውን መግቦተ እግዚአብሔር የሚያዘምሩት ልጆች በቅዱሳን ሐዋርያት፥ታሪክን ከምሥጢር ያስተባበረው ዜማቸውም በቃለ ሰብከታቸው፥ከየቤቱ የሚሰጣቸው ሙልሙል ዳቦም /ኅብስት/ ጌታችን በማቴ.10፥5–11 «የእሥራኤል ቤት ወደሚሆኑት በጎች ሂዱ።...መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ። ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ፥ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና።» ሲል ለሰብከተ ወንጌል የተሰጣቸውን መመሪያ ያዘክራል። እንደሚታወቀው እናቶች ለዚህ በዓል የሚሆን ዳቦ ለመጋገር /የሚከበረው በዳቦ ነውና/ ስንዴያቸውን ሲያጥቡ፥ሲፈትጉ፥ሲያስፈጩ ይሰነብታሉ። በበዓሉ ዋዜማም የየሠፈሩ ሕፃናት ከላይ በተገለጠው መልክ ሲጨፍሩ እናቶች ካዘጋጁት ሙልሙል ዳቦ እያነሡ ይሰጧቸዋል። ጭፈራው ሲያበቃም ሙልሙል ዳቦአቸውን እየገመጡ ሲጫወቱ ይውላሉ። በተጨማሪም የቡሄ ዕለት ለዘመድ ላዝማድ እያንዳንዱ ቤተሰብ በልጆቹ ልክ ዳቦ ይሰጣል። ለክርስትና ልጅ፥ለጡት ልጅ፥ለአማች ልጅ ፥ለሞግዚት በየቅርብ ዕውቂያ ላለውም ሁሉ የቡሄ ዳቦ ይላካል። /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ 1986 ዓ.ም. ፥ገጽ 128/።

አስቀድመን እንደገለጥነው ይህ የብርሃን መለኮት በዓል በቤተ ክርስቲያናችን የአብነት ት/ቤት ያሉ ደቀ መዛሙርት በዓልም ጭምር ነው። እንዲያውም ሲቃውንት ቤተ ክርስቲያን የደብረ ታቦርን በዓል «የተማሪ /የተማሪ/ ዝክር» እያሉ ይጠሩታል። ይህም ያለ ምክንያት አይደለም። እንደሚታወቀው ጥንታዊው የአብነት /የቆሎ/ ተማሪ የድንቁርናን ጨለማ በዕውቀት ብርሃን

www.ethiopianorthodox.org

የሚያርቀው፣ ምሥጢርን የሚያገምረው /የሚያደላድለው/ የትውልድ አገሩን ትቶ፣ወንዝ ተሻግሮ፣ከውሻ ተከላክሎ፣ቁራሽ እንጀራ ለምኖ፣ደበሉኖ ማቅ ለብሶ፣ተርቦ ተጠምቶ፣አይመስሉ መስሎ፣ቀይ የነበረው ጠቁሮ፣በዋትወ መከራን ሁሉ ታግሦ ነበር። እንዲሁም ስለሆነ የመናኞች ፈታውራሪ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሲሆኑ ማቁን ጨርቁን ሳይሉ ከወገንና ከዘመድ ሳይለናበቱ ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት «የፈቃድ ስደተኛ» የሆኑት ደቀ መዛሙርት እናትና አባታቸውን፣ሥራቸውንና ሀብታቸውን ጥለው መድኃኔዓለም ክርስቶስን በእግር በተከተሉት በግብር በመሰሉት ቅዱሳን ሐዋርያት /ዮሐ. 6፥67–69፤ ሉቃ.6፥13–19/ ይመሰላሉ። በዓሉንም መዘከራቸው ጌታ በታቦር ተራራ ላይ ክብረ መንግሥቱን ብርሃን መለኮቱን ለሦስቱ የምሥጢር ደቀ መዛሙርት በተከሰቶ /በግልጥ/ ለተቀናት ለስምንቱ ሐዋርያት (በት.ኢሳ.26፥10 ላይ ለኃጢአተኛ ሞገስ ቢደረግለት ጽድቅን አይማርም… የእግዚአብሔርንም ግርማ አያይም በተባለው መሠረት የአስቆሮቱ ይሁዳን አሳልፎ የሚሰጠው ነውና እርሱን አይጨምርም።) በጸጋ እንደ ገለጠላቸው ለእነርሱም የጸዋትወ ዜማን፣የቅኔንና የመጻሕፍትን ምሥጢር እንዲገልጥላቸው፤ ቀለም እምቢ እንዳይላቸው፥ ባሰቡት ሰዓት ተምረው ለአገራቸው፣ ለቤተ ክርስቲያናቸው እንዲበቁ፣ወጥተው እንዳይቀሩ በማመን ነው። እግረ መንገዳችንን ከአራቱ ቤተ ጉባኤያት ቅኔ የተጀመረው በአምስተኛው መቶ ዓ.ም. በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ይሁን እንጂ ግጥም ገጥሞ ምሥጢሩን ረቀቅ አድርጎ ሰሙንና ወርቁን ለይቶ መቀኘት የመጣው በ1408 ዓ.ም በነበረው ዮሐንስ ገብላዊ /ዘፍልሱፍ/ በሚባለው ሊቅ ነው። ይህ ሊቅ አገባቡን ጨምሮ የቅኔን ምሥጢር ለማግኘት ሱባኤ ገብቶ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠለት የዓዲ ይኩኖ አምላክ ከተማ በነበረችውና በአማራ ሳይንትና በቦረና መካከል በምትገኘው በደብረ ታቦር መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን። [በሊቀ ማእምራን ዕንባቆም ቃለ ወልድ፤ ስለ ቅኔ ትምህርትና ስለ ጥቅሙ፤ ለሦስተኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ የቀረበ።]

ስለ አከባበሩም፥ በሁሉም ቤተ ጉባኤያት የሚዘከር ቢሆንም፤ የአከባበሩ ሁኔታ /ቅድመ ዝግጅት/ ግን ከቦታ ቦታ መጠነኛ ልዩነት ይታይበታል። በደቡብ ጎንደር /እንዳቤት፥ስማዳ/ እንዲሁም በምዕራብ ጎጃም አካባቢ፥ ተማሪው የሚያስተዳድረው የቡድን፥ የቡድን አለቃ አለው፤ በአለቃው በኩል ብር ያዋጣል ወይም ገበሬው ዘር በሚዘራበት ወቅት «ተሥዒንን ዘወንጌለ ቃለ፥ የወንጌል ቃል ተጫምተን መጣን» በሚል የቸብቸቦ ዜማ እየዞሩ «በእንተ ስማ ለማርያም፥ስለ ደብረ ታቦር ብለም» ሲሉ ባሕሉ ይታወቃልና ጌሾ፣ስንዴ፣ገብስ፣ባቄላ የመሳሰሉት በገፍ ይሰጣቸዋል። ከዚህ ሁሉ ጋር ተማሪዎቹ በኅብረት ሆነው የአርሶ አደሩን ማሳ አረም አርመው፣ቁፋሮ ቆፍረው የጠላና የዳቦ እህል፥ በጋን ጠላ የቻለም ገንዘብ ይሰጣቸዋል። በአንዳንድ ቀበሌም ተማሪዎቹ ራሳቸው የጉልበታቸውን ዋጋ በበዓሉ ዕለት የሚያስፈልገውን ሁሉ በቤታቸው አዘጋጅተው ይዘው እንደሚመጡላቸው ቃል ይገቡላቸዋል። ብዙውን ጊዜ ግን ጠላውን የሚጠምቀው፥ቆሎውን የሚቆላው፥ ንፍሮውን የሚቀቅለው፥ ዳቦውን እንደ አነባበሮ አድርጎ የሚያዘጋጀው ተማሪው ራሱ ነው። ጠላውን ለመጥመቅ ለመበለቶች የሚሰጡ ቢኖሩም የጉልበት ሥራውን የሚሠሩት ግን ተማሪዎቹ ራሳቸው ናቸው። በዋድላና በአማራ ሳይንት አካባቢ ለበዓሉ የሚታሰበው ከጥር ወር ጀምሮ ነው። ከጥር ወር በኋላ ወደ ቤተ ጉባኤው የሚገባ እንግዳ ተማሪ «ተሜ፥እንዴት ነው፤ ትከርማለህ፥ ደብረ ታቦርን ትዘክራለህ?» ተብሎ በተማሪዎች የቡድን አለቃ ይጠየቃል፤ የሚከርምና ደብረ ታቦርን የሚዘክር ከሆነ «መንደር ይሰጠኝ» ብሎ ለአለቃው ያመለክታል። አለቃውም ለመምህሩ «እያ እገሌ መንደር ይሰጠኝ ብሏል።» ብሎ ይጠይቅለታል። መምህሩም የተማሪውን ሁኔታ አስጠይቀው /ዓይኑ ስውርና የአካል ጉዳተኛ፣ ፈሪና ደካር…መሆን አለመሆኑን መር ምረው/ መንደሩን /ቅፈቱን/ ይፈቅዱለታል። በተደ ለደለበት መንደር እየዞረም «የደብረ ታቦር በዓል አለብኝና የቆሎ፥የጠላ፥የዳቦ እህል እንዲችሉኝ» ብሎ ያስታውቃል። እነርሱም በሚችሉት መጠን ቃል ይገቡለታል። መንደር ሳይደለደል የቆየ ተማሪ እንኳን ቢኖር ከሰኔ እስከ ነሐሴ የሚደርስ የበልግ አዝመራ ወዳለበት ወደ ደጋው አገር ለአራትና ለአምስት ሰዓታት በእግሩ ተጉዞ ሲለምን ከአውድ ማው እየ ታፈሰ ለበዓሉ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ጊዜ የሚተርፍ ቀለብ ይዞ ይመ ለሳል። የሐዋርያቱን የቅዱስ ጴጥ ሮስን፥የቅዱስ ያዕቆብንና የቅዱስ ዮሐንስን ስም እያነ ሡ «ሆያ ሆዬ» ብለው ለበዓሉ የሚያስፈልገውን የሚ ሰበስቡም አሉ። በዓሉ ሲቃረብ ተማ ሪው በምድብ በምድብ ሆኖ ሥራ ይከፋፈላል፤ ጠላ በመጥመቅ ንፍሮ በመቀቀል ፥ቆሎ በመቁላት ዳቦ በመጋገር። በደብረ ዓባይ «ደብረ ታቦርን እዘክራለሁ» ብሎ ቃል ተገባ በኋላ በራሱ ጉዳይ ለመሰናበት የተነሣ ተማሪ «እኔ እገሌ ይዘክሩ ልኝ» ብሎ ለማኅበሩ ተናግሮ የድርሻውን ሰጥቶ ካልሄደ ማኅበረ ደቀ መዛሙርቱ ያዝኑበታል። በመርጡለ ማርያም የሆነ እንደሆነ ትምህርት ቤቱ ከተማ አካባቢ ስለሆነ ተማሪዎቹ የቀረውን በራሳቸው አያዘጋጁ ጠላ የመጥመቁን ተግባር ግን ከዘለሞያ ከለባም ሴት /ጥሩ ጠማቂ/ ጋር ውል ይገባሉ። ለመጠጡ ማማርም ሆነ መበላሸት ተማሪው ተመሰጋኝም ተወቃሽም ስለሆነ ገና ከድፍድፍ ጀምሮ እየቀመሰ ያስጠምቃል።

በዶሩ ባይነገርም እንኳን የደብረ ታቦር በዓል የደቀ መዛሙርት /የተማሪዎች/ ዝክር መሆኑን ሁሉ የምትጠብ ሕዝብ እንኳን ታውቃለች ስለሚባል «ብሬ የተሜ ዝክር ነው» እያሉ የደብረ ታቦር በዓል ዕለት ለማ ስቀደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ምእመናን መሰብሰባቸው አይቀርም። የገጠር ቤተ ክርስቲያን እስከ ስድስትና ሰባት ደጅ ሰላም ያለው ነውና ምእመኑ በየሰንበቴው ማኅበር ተከፋፍሎ በየማዕረጉ እንዲቀመጥ ይደረጋል። አልያም በመንደሩ የሚዘክ ራቸውን ተማሪዎች ስለሚለይ እነርሱ በሚያስተናግዱበት ምድብ ይገባል። አስተናባሪው /አስተማሪ/ ተማሪው ብቻ ነው።

አንዳንድ ምእመናን አዘውትረው ለሚዘክሩት ተማሪ «ቡሄ ነው» እያሉ የዕለቱ ዕለት የሚያበረክቱ አሉ። መስተንግዶው ይቀጥላል። በንግሩችን ላይ ለመስተንግዶ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን ጭምር ነው ተማሪው ከምእመኑ የሚዋሰው። የዝክሩ ሂደት እንደተጠ ናቀቀ ከምእመናን መካከል ያሉ ሽማግሌዎች ተነሥተው ምርቃቱን ያዥጎደጉዱታል። ከሆነቱም ዕለቱን በተመለከተ ትምህርታቸውና ቡራኬያቸው ያሰርጉታል። በመጨረሻው ለበዓሉ ዝግጅት ልዩ አስተዋፅ ሳደረጉ ምእመናን ወደ ማታ ላይ ወደ ቤተ ጉባኤ እንዲመጡ ልዩ ጥሪ ይደረጋል። በዚህም መስተንግዶ እየተካሄደ ድጓ የሚያውቀው ያሬ ማል፥አቋቋም የሚያውቀው በዝማሬ በጸናጽል በመቋሚያ ይዘምራል /ይወርባል/፥ቅኔም የሚያውቀው ከመምህሩ ጀምሮ እንደ ችሎታቸው መጠን በዓሉን የተመለከቱ ቅኔዎችን ያበረክታሉ።

በዓሉ እንዲህ በአንድ ቀን ብቻ የሚከተት ሳይሆን እንደ ዝግጅቱ መጠን ከሦስት እስከ ሰምንት ቀናት ይቆያል። በእነዚህ ቀናት እያንዳንዱ ተማሪ ለቡሄ ተብሎ ከመጣለት ኅብስት ሳይሰስት እየተካፈለ ይቃመሳል። እንዲያውም ስስት እንዳይኖር በዚህ ሰሞን የሚሰጠው ትምህርት የሐዋ.ሥራ 5፥1–11 ላይ የተዘረዘረው በንፍገታቸው የተቀጡት የሐናንያና የሚስቱ የሰጲራ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም በዓሉ

www.ethiopianorthodox.org

በዘመነ ሐዋርያት የነበረውን የፍቅር ማዕድ /AGAPE/ ያስታውሰናል:: በመሆኑም የቅኔው ተማሪ የዜማውን፣ የዜማውም ተማሪ የአቋቋሙን፣ የአቋቋሙም ተማሪ የቅኔውን «ዛሬ እኛ ጋር እንድትመጡ !» እየተባባሉ ይገባበዛሉ:: መምህራንም ድግሱ እስከለቀ ድረስ በየግብዣው ላይ እየተገኙ ትምህርትና ቡራኬ ሲሰጡ ይሰነብታሉ:: በአጠቃላይ ደብረ ታቦር (ቡሄ/ሔ/) -በተመጽዋችነቱ /በተዘካሪነቱ /የሚታወቀው ተማሪ በፈንታው የሚዘክርበት፣ የተማሪ ክብሩ የሚገለጥበት፣ ስእለቱ የሚፈጸምበት ተናፋቂ የደቀ መዛሙርት በዓል ነው:: ይኸውም እስከ ዛሬ ድረስ በመንፈሳዊ ት/ቤቶች የሚሠራበት ነባር ትውፊታችን ነው:: (ከልዩ ልዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የቃል አስረጅዎች የተገኙ)

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በታዘበው መጠን በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አድባራትና ገዳማት መካከል፤ ለፍልሰታ ለ ማርያም ጾም ለማስተደስ ከሚመጡ ምእመናንና ከገዳሙ ነዋሪዎች በተገኘ ተዋፅዖ የቡሄ/ሔ/ ወይም የደብረ ታቦር በዓል በድምቀት የሚከበረው በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳምና በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን፤ በውስጣቸውም በሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶችና የአብነት ትምህርት ተ ማሪዎች ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ ዛሬ ዛሬ በተለይ በከተሞቻችን /በገጠሩም ቢ ሆን/ የቡሄ/ሔ/ በዓልን የሚያከብሩ ብዙ ልጆች የበዓሉን ጥንተ ታሪክና የአከባበር ዘይቤ አያውቁትም ማለት ብቻ ሳይሆን «የባንቲም ማትረፊያ» አድርገውታል ለማለት ያስደፍራል:: «ለጭፈራው» የሚጠቀሙበት ከንቱ ውዳሴ በስብሐተ እግዚአብሔርና ከበዓሉ ታሪክ ጋር ግጥም ካለመሆኑም በላይ ታዋቂ ስፖርተኞችን ድምፃውያንን፣የፊልም ተዋንያንን ወዘተ ስሞች እየጠቀሱ «የሚያሞግሱበት» ነው:: አንዳንዱም «ከሰጡን እንሪዳ+ ከነሱን እናሪዳ» እንዲሉ ስድብ፣ርግማንንና ዘለፋ የሚያከሉበትም አሉ፤ የፈረንጆቹን ችቦ /fire works/ እያቀጣጠሉ በየመንገደኛው ጫማ+የዕቃ መያዣና የእንግት ቦርሳ እንዲሁም ኪስ ውስጥ በመጨመር የሚያውኩም አይጠ ፉም:: ይህ «ጭፈራና ሁካታ» ከበዓሉ ትክክለኛ ቀን በፊትና በኋላም የሚጀመርና የሚቀጥል ነው:: ይህ ሁሉ ከትውፊታችን ውጭ መሆኑ እሙን ነው:: እንግዲህ መቼም ያልዘሩትን ማጨድ አይቻልም፤ በከተሜዎቹ ደቂቃን ላይ ለማማረርም ኅሊናዊ /ሞራላዊ/ መሠረት ያለን አይመስለኝም:: እናስ?

እናማ የበዓሉ ጥንተ ታሪክ /ዝክረ ነገር/ ወደ ትዝታ ከመለወጡ በፊት:-

- የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤያትና ሰንበት ት/ቤቶች በአንዳንድ አድባራትና ገዳ ማት ከሚታዩ መልካም ተሞክሮዎች /ልምዶች/ ተመልክተው እነርሱም እንዳሉበት ተጨባጭ ሁኔታ /አቅም/ በዓሉ ሥርዓቱንና ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከበር የሚያስተባብሩበት ጥረት ቢኖር፣ ማኅሌታዊ ቅዱስ ያሬድ «ሰባሕኩከ በደብር በቅድመ ሙሴ ወኤልያስ ነቢያት ምእመናኒከ፤ በታማኞችህ ነቢያት በሙሴና በኤልያስ ፊት በተ ራራ /በቤተ ክርስቲያን/ አመሰገንኩህ» እንዳለ::
- የግጥምና የዜማ መድረስ ዝንባሌ /ክ ሂል/ ያላቸው ምእመናንና በዘርፉ የደከሙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በበዓሉ ዙሪያ ዜማዎችን እያዘጋጁ፤ በመደባቸው /በመሠረታቸው/ የቤተ ክርስቲያኒቱን የዜማ ሥርዓት በጠ በቀ መልኩ ቢዘምሩና ቢያዘምሩ፤ በድምፅ+በምስልና በጽሑፍ የኅትመት ውጤቶች ቢያሠራጩ፤
- ከቤተ ክርስቲያን ተቋማዊና ከሊቃውንቱ ሞያዊ ጥረት ጋር የበዓ ሉን ትውፊታዊ የአፈጻጸም ሥርዓት ከመጠበቅና የወላጆች ቤተሰባዊ ኃላፊነት በአከባበሩ ረገድ አሁን የሚስተዋለውን የሥነ ምግባር ጉድለት ከመሙላት አኳያ ያለው ድርሻ የማይናቅ ነው:: «ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትመጡ ልጆቻችሁን ይዛችሁ ኑ፤ ብቻችሁን አትምጡ፤ ብቻችሁን ከመጣችሁ ልጆቻችሁ ወደ ሌላ ይሄዳሉ::» /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/::
- ከተገለጡት የመፍትሔ ሐሳቦች አንጻር በዓሉ ነባር የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ቢሆንም በአከባበር ረገድ ግን በተወሰኑ የአገሪቱ አካባቢዎች ብቻ የተወሰነና በአመዛኙም ባሕላዊ መልክ ብቻ ያለው /በባሕላዊ ገጽታውና ስሙ የዳበረ/ መስሎ ይታያልና፤ ከጌታችን ዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ የሆነው ይህ የብርሃን በዓል ቤተ ክርስቲያናችን /ምእመናነ ክርስቶስ/ ባሉበት ሥፍራ ሁሉ የሚዘከርበት ሁኔታ ቢኖር መልካም ነው፤ ከመንግሥታዊና ከግል የሥራ ተቋማት የሥራ ዝቢታ ተወግደን /ታቅበን/ በዕለቱ እንድናርፍ የቀን መቁጠሪያ ካላንደር ላይ «ቀኑ ቀልሞ» ብሔራዊ በዓል ሆኖ ባናየውም በሩቅም በቅርብም፤ በተናጠልም በጋራም በያለንበት ት[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ይህንን ያህል ካልን ለጽሑፉ መቋጫ የምናደርገው የመለከት መጽሔት በነሐሴ ወር 1991 ዓ.ም በ7ኛ ዓመት ቁጥር 6 እትሙ «ቡሄ የደብረ ታቦር ትዝታ» በሚል ርእስ ካሰፈረው ጽሑፍ ያካተተውን «የቡሄ መዝሙር ግጥም» በማስታወስ ይሆናል:: የቅዱሳን ነቢያትና የቅዱሳን ሐዋርያት አምላክ የበዓሉን መንፈሳዊ ይዘት ጠብቀን በማክበር በበረከቱ እንዲያትረፈርፈን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን::

ሆያ ሆዬ ሆያ ሆዬ
ሆይ የኛ ጌታ መድኃኔዓለም
አባክህ ስጠን ፍቅር ሰላም
ሆያ ሆዬ ዝና
በእምነት እንጽና
በደብረ ታቦር ሆ የተገለጠው
የሁሉ ጌታ ሆ መድኃኔዓለም ነው
ብርሃን ታየ ሆ በተራራ ላይ
ጌታ ፈጣሪ ሆ የሁሉ ሲሳይ
እዝ ...
ያዕቆብ ዮሐንስ ሆ እንዲሁም ጴጥሮስ
አምላክን አዩት ሆ ሙሴ ኤልያስ
አባቱ አለ ሆ ልጄን ስሙት
ቃሌ ነውና ሆ የወለድኩት
እዝ...
ታማልዳለች ሆ ድንግል ማርያም
አይጠራጠር ሆ ይመን ዓለም
ጻድቃን ቅዱሳን ሆ ያማልዳሉ
ፍጥረትህን ማር ሆ አድን እያሉ
እዝ...
ኢትዮጵያውያን ሆ ታሪክ ያላችሁ
ባሕላችሁን ያዙ ሆ አጥብቃችሁ
ችቦውን አብሩት ሆ እንዳባቶቻችሁ
ምሥጢር ስላለው ሆ ደስ ይበላችሁ
እዝ...
ለድንግል ማርያም ሆ አሥራት የሆንሽ
ጻድቃን ቅዱሳን ሆ የሞሉብሽ
በረከታቸው ሆ ያደረብሽ
ሁሉም እንግዶች ሆ የሚያርፉብሽ
ሀገረ እግዚአብሔር ሆ ኢትዮጵያ ነሽ
እዝ...
ለሐዋርያት ሆ የላከው መንፈስ
ዛሬም ለኢትዮጵያ ሆ ጸጋው ይዳረስ
በበጎ ምግባር ሆ እንድንታደስ
በቅን ልቡና ሆ በጥሩ መንፈስ
የአምላክ በረከት ሆ ለሁላችን ይድረስ

እዝ...

ዓመት ዓውደ ዓመት ድገምና
ዓመት ድገምና
ኢትዮጵያ እንድታገኝ ድገምና
ሰላም አንድነት ድገምና
ገበሬም እንዲያገኝ ፍሬ በረከት
ክብር በምግባር ጽና በእምነት
በነፍስ እንዳትሞት::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር